ስርዓተ ነጥቦች

1. አንድ ነጥብ ወይም ያዘት(.)

ቃላትን በምህጻረ ቃል አሳጥሮ ለመጻፍ ያገለግላል።

ምሳሌ፦ ኢ.መ.ማ (የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር)

ብርን ከሳንቲም ለመለየት ያገለግላል።

ምሳሌ፦ 5.25 (አምስት ብር ከሀያ አምስት ሳንቲም)

ሙሉና ሸርፍራፊ ቁጥሮችን ለመለየት

ምሳሌ፦ 3.5 (ሶስት ነጥብ አምስት)

2. ሁለትነ ጥብ(፡)

ቃልን ከቃል ለመለየት

ምሳሌ፦ ትምህርቴን፡በርትቼ፡አጠናለዉ።

ሰዓትን ከደቂቃ ለመለየት

ምሳሌ፦ 3፡20 (ሶስትሰዓትከሀያ)

3. አራትነጥብ(።)

ዓ.ነገርን ለመደምደም ያገለግላል።

ከዓ.ነገር መጨረሻ በመግባት ዓ.ነገርን ይቋጫል።

ምሳሌ፦ እናቴ ሸሚዝ ገዛችልኝ።

4. ቅንፍ ( )

ወይም የሚለዉን ቃል ይተካል

ምሳሌ፦ ብዙ (በርካታ)

5. የጥያቄ ምልክት ?

በመጠይቃዊ ዓ.ነገር መጨረሻ በመግባት ዓ.ነገሩ መልስ የሚፈልግ መሆኑን ያመለክታል።

ምሳሌ፦ መቼ መጣህ?

6. ትዕምርተስላቅ

ምፀትንና ማሾፍን እንዲሁም ተሳልቆትን ያመለክታል።

ምሳሌ፡ ልብስህን ቅደደዉ ይሰፋልሀል

7. ትዕምረተ ጥቅስ “ “

አባባሉ የሌላ ሰዉ መሆኑን ለማመልከት

ምሳሌ፦ “ማርፈድ የስንፍና ምልክት ነዉ” አሉ መምህሩ።

8. ቃል አጋኖ ወይም ትዕምርተ አንክሮ !

ቁጣን፣ አድናቆትን፣ደስታን፣ ጩኸትን፣ ንዴትን ወዘተ ለመግለፅ ያገለግላል።

ምሳሌ፦ ቤቱ ፈረሰ ያስጋልባል!

9. ነጠላ ሰረዝ ፣

ተመሳሳይ ተግባር ያላቸዉን የቃላት ድርድሮችን ለመለየት

ምሳሌ፦ እናቴ ከሱቅ ስኳር፣ ፓስታ፣ ዘይትና መኮረኒ ገዛች።

10. ድርብ ሰረዝ፤

አያያዦችን በመጠቀም ነጠላ ዓ■ነገሮችን ለማጣመር ያገለግላል።

ምሳሌ፦ ማረፍ እፈልጋለዉ፤ ቢሆንም ሰራዬን አልጨረስኩም።